# ሞትና ትንሣኤ

መ/ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን



በዚች ምድር ላይ የምንቆይበት ጊዜ የተወሰነ ነው። በጣም አጭርም ነው። መጻሕፍትም፣ ሊቃውንትም እንደ ጥላ፣ እንደ ጤዛ ያለ ነው ብለውታል፣ በሌላም ገጽ የዚህን ዓለም የቆይታ ኑሮ የእንግድነት ጊዜ እንደ ሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል። «...እኔ ለጥቂት ጊዜ ያንተ እንግዳ ነኝ እንደ ቀድሞ አባቶቼም በስደተኛነት የምኖር ነኝ» (መዝ.፴፱፥፲፪)። ከአዳም እስከ ኖኅ በነበረው ዘመን ሰዎች ወደ አንድ ሺህ ዓመት የተጠጋ ዕድሜ እንደ ነበራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦአል። (ዘፍ.፭፥፩–፴፪) ከዚያ በመለስ እስከ አምስት መቶ ዓመት ዕድሜ የተሰፈረላቸው አበው ለዚህ አጭር ጊዜ ቤት አንሠራም ብለው ኑሮአቸውን በዳስ፣ በሰቀላ፣ በድንኳን አሳልፈዋል። ምሥጢሩ አንድና አንድ ነው፣ ሺህ ዓመትም ተኖረ መቶ ዓመት መጨረሻው ሞት ስለ ሆነ ነው።

ሞት የተፈጠረው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች በገነት ሳሉ የተሰጠውን ፈተና ተቋቁመው ማለፍ ተስኖአቸው በወደቁ ጊዜ ነው። በተሰጡት አለመርካት፣ ያልተሰጡትን መሻት፣ ለአደራ አለመብቃት፣ ምን ጊዜም አደጋ አለው፣ በበለስዋ ፍሬ አካባቢ በተፈጸመው ስሕተት ኃጢአት በሰው ሕይወት ሠርፆ ሞተ ሥጋ፣ ሞተ ነፍስ በወሪደ መቃብር ወሪደ ገሃነም ተፈረደ። ኃጢአት ማለት የተሰጡትን፣ የተቀበሉትን፣ እጅ የገባውን ሀብት፣ ክብር፣ ፀጋ ማጣት ማለት ነው።

በመጀመሪያዎቹ ሰዎች በደል የተፈረደው ፍርድ በሰው ዘር ሁሉ ተላለፈ፣ ከአዳም እስከ ሙሴ የነበሩ ሰዎች በሞት ጥላ ሥር ኖሩ፣ ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ የተገለጠው በሰው ላይ የፈሰሰውን የተፈረደውን የፍርድ መርገም አጥፍቶ፣ ኃጢአትን ከሥሩ ነቅሎ፣ አስወግዶ የሞትን ሰንሰለት ፈትቶ፣ ከእግዚአብሔር የተለዩትን ከተድላ ገነት የወጡትን፣ ከፀጋ ልጅነት የራቁትን፣ ወደ ቀድሞ ነፃነታቸውና ክብራቸው ለመመለስ ነው። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ ኮረብታ በዕለተ ዓርብ በተሰቀለ ጊዜ ኃጢአት ከሥሩ ተነቅሎ ወድቋል፣ ሞት በክርስቶስ ሞት ተሽሮአል።

በዓለማችን ስንኳን ለክፉ ሰዎች ለደጋግ ሰዎችም የሚሞት የለም። እጅግ የሚወደዱ ቢኖሩ ፍቅራቸው እስከ መቃብር ነው የሚጓዘው። የሞትን ክልል አልፎ ከመቃብር አድማስ ማዶ የሚሻገር የለም። የሁሉም ሽኝት እስከ መቃብር ነው። የአንደበት ሽንገላና ውዳሴ ከንቱ በተመላች ምድራችን «አንተ ቁምልኝ እባክህ፣ በሞቴ ልቅደምህ» እየተባለ የተዘመረላቸው፣ የውዳሴ ቅኔ የቀረበላቸው ሰዎች ነበሩ፤ የሞት መጥሪያ እየደረሳቸው በተጓዙ ጊዜ ግን የቀደመላቸው የተከተላቸውም የለም፣ ለብቻቸው እንደ መጡ ብቻቸውን አልፈዋል።

ክርስቶስ ሰውን የወደደበት ፍቅሩ ከሰው የሚለየው በዚህ ነው፣ የሚጠሉትን መውደድ ለበደሉት ራስን ካሣ አድርጎ መስጠት፣

«ለክፉ ሰዎች በጭንቅስ እንኳ ይሞት ዘንድ የሚወድ አይገኝም፣ ለደጋጎች ሰዎች ይሞት ዘንድ የሚወድ ይገኝ እንደ ሆነ እንጃ፣ ክርስቶስ እኛ ኃጢአተኞች ስንሆን ስለ እኛ ኃጢአት ሊሞት በጊዜው ጊዜ መጣ» ብሎ አል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (ሮሜ. ፭፥፯–፰)።

በአንድ አዳም በደል ብዙዎች ሞት እንደ ተፈረደባቸው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ሆነ፤

«የመጀመሪያው ሰው አዳም ከምድር የተገኘ መሬታዊ ነው፣ ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ግን ከሰማይ የመጣ ሰማያዊ ነው፣ አዳም መሬታዊ እንደ ሆነ እኛም መሬታውያን ነን፣ ክርስቶስ ሰማያዊ እንደ ሆነ እኛም ሰማያውያን ነን፤ የዚያን የመሬታዊውን መልክ እንደለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።» (፩ቆሮ. ፲፭፥፵፯–፵፱) የትንሣኤ ምሥጢር በዚህ ይገለፃል።

በጥንተ ፍጥረት «አትንኩ ጠብቁ» የተባሉትን አክብሮ ጠብቆ በጥቂት ዘመን ትዕግሥት ፈተናውን ማለፍ ቢቻል ኖሮ ውጤቱ በየሺህ ዓመቱ እየታደሱ ከሕይወት ወደ ሕይወት መሸጋገር ነበር። የሞት መልክ ሳይታይ የልቅሶና የዋይታ ድምፅ ሳይሰማ ወደ ዘለዓለም ተድላ መግባት በተቻለ ነበር። ዕንቅፋት ያልነበረው የሕይወት መንገድ በኃጢአት ስለ ተደናቀፈ ወደ ዘለዓለም ሕይወት መድረስ የሚቻለው በሞት በኩል ታልፎ በሚገኘው ትንሣኤ ነው። በአዳማዊ ባሕርይ የምንንቀሳቀስ ሰዎች ሁላችን እንሞታለን፣ ወደ ተገኘንበት መሬት እንመለሳለን። ነገር ግን ሥጋዊ ሞት የመጨረሻ ሞት አይደለም፣ ከሕይወት ወደ ሕይወት መሸጋገሪያ



www.ethiopianorthodox.org

ድልድይ ነው። የነፍስ ማኅደር የሆነው ሥጋችን እንደ ቀን (እንደ ሥራ) ልብስ ነው። ሥራ ሠርተን በምናልፍበት በዚህ ዓለም እሱን ለብሰን እንንቀሳቀሳለን፤ ዕድሜ የምንለው የቆይታ ጊዜ እንደ ፀሐይ ሲጠልቅ ወደ ነፍሳችን ዕረፍት ስንመለስ አውልቀን በመቃብር እናኖረዋለን። እስከ መጨረሻው የሙታን ትንሣኤ በዚያው ይቆያል። ነፍስ ግን ወደ ፈጣሪዋ ትመለሳለች።

በዚህ መልኩ ሁላችን የሞት እንቅልፍ እናንቀላፋለን፤ ነገር ግን የተኛ ሰው ፈጥኖ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ በኋለኛው ዐዋጅ ፈጥነን እንነሳለን፤ ፈጥነን እንለወጣለን ይህም ታላቅ የሙታን ትንሣኤ ምሥጢር ነው።

«ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፤ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና» (፩ቆሮ.፲፭፥፶፫)።

ጌታችን በታቦር ተራራ ላይ ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበት ጊዜ ሙሴ በሞት፤ ኤልያስ በዕርገት ከዚህ ዓለም ከተለዩ ብዙ ዘመን በኋላ ሙሴ ከሞት ተነስቶ ከመቃብር ወጥቶ፤ ኤልያስ ከብሔረ ሕያዋን መጥቶ በሕይወተ ሥጋ ከነበሩ ሐዋርያት ጋር ትንሣኤና ሕይወት በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት መገናኘታቸው የሙታን ትንሣኤ ማረጋገጫ ሌላው ትምህርት ነበር። እነሆ «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል የታመነ ይሆን ዘንድ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በመሬት ውስጥ ወድቀው ሥጋቸው የፈረሰ፤ አጽማቸው የተከሰከሰ፤ እንደ ሣር እንደ ገለባ የተበተኑት ሁሉ ይነሳሉ። በመጨረሻው የሙታን ትንሣኤ በሚደረገበት ጊዜ:-

በመጀመሪያ ዐዋጅ የተበተነ ሥጋ ሁሉ ይሰበሰባል፤

በሁለተኛ ዐዋጅ አጥንት ከአጥንቱ ይሳካል ይመሳኳል፤

በሦስተኛ ዐዋጅ ሙታን ከቁጥራቸው ሳይጐድሉ አካል ሳይጐድላቸው በአዲስ አካል ይነሳሉ። (ቅዱ. ያዕ.ዘሥ)

ይህም አስቀድሞ በነቢይ ተነግሮአል:- «የሰው ልጅ ሆይ በእነዚህ አጽሞች ላይ ትንቢት ተናገር፤ የደረቃችሁ አጥንቶች ሆይ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ስሙ በላቸው። ...እነሆ እኔ መቃብራችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁ አወጣችኋለሁ፤ ነፍስ አዋሕጄ አስነሳችኋለሁ፤ መጀመሪያ ዥማት እታታብችኋለሁ፤ ሁለተኛ ሥጋ እመርግባችኋለሁ፤ ሦስተኛ ቁርበት አለብሳችኋለሁ፤ አራተኛ ነፍስ አዋሕዳችኋለሁ፤ ወዲያው ትነሳላችሁ» ተብሎ። (ሕዝ.፴፯፥፩-፲፪)።

በነቢያት የተነገረው፤ በራእይ የተገለጠው፤ በተአምራት የታየው ሁሉ በክርስቶስ ትንሣኤ ታትሞ ተረጋግጦአል። ክርስቶስ በሞት ላንቀላፉት ሁሉ በኩር ሆኖ ተነስቶአል።

በመዋዕለ ትምህርቱ ምልክት እንሻለን ብለው ለጠየቁት ማስረጃ አድርጎ የሰጣቸው የዮናስን ታሪክ ነበር።

«ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ኖረ እንዲሁ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ያድራል» የሚል ነበር (ማቴ.፲፪፥፴፰-፵)።

በክርስቶስ የስቅለት ሞት የፈረዱ ጸሐፍት ፈሪሳውያን መቃብሩ በባለ ሥልጣኖች ፊርማና ማኅተም እንዲታሸግ ንቃት፤ ትጋትና ኃይል ባላቸው ወታደሮች እንዲጠበቅ አድርገው ነበር። ነገር ግን ክርስቶስን ከመነሳት ያገደው ምንም ኃይልና ሥልጣን አልነበረም።

- በመቃብሩ ላይ ተገጥሞ የነበረው ድንጋይ ተገለባብጦ ተገኝቶአል፤
- በመቃብሩ ራስጌና ግርጌ የነበሩ ቅዱሳን መላእክት «ሕያውን ከሙታን ጋር ለምን ትፈልጉታላችሁ፤ ከዚህ የለም ተነስቶአል» ብለው መስክረዋል።
- በዚያው አካባቢ ሌሊቱን ሲመላለሱ ያደሩ ቅዱሳት አንስት (ሴቶች) በአካል አይተውታል።
- ራሱ ጌታ «እነሳለሁ» እያለ ከመሞቱ በፊት የተናገረው ተፈጽሞ ለደቀ መዛሙርቱ ተገልጦ ታይቶአል፤ ዓርባ ቀንም አብሯቸው ሰንብቶአል።
- እነ ቅዱስ ጳውሎስም ከትንሣኤው በኋላ በግልጽ ማየታቸውን አረጋግጠዋል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት ይቻላል።

ማቴ.፲፯፥፲፯፤ ሉቃ.፳፬፥፫-፯፤ ዮሐ.፳፩፥፲፬፤ ማቴ.፳፰፥፰-፳፤ ፲፯፥፬፤ የሐዋ.፪፥፴፩፤ ፬-፴፫፤ ፩ቆሮ.፲፭፥፫-፳።

አዎ ክርስቶስን ሞትና መቃብር ይዘው ሊያስቀሩት ስላልቻሉ ሦስት መዐልትና ሦስት ሌሊት በመቃብር አድሮ ሞትን፤ ኃጢአትን ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ተነስቶአል፤ ሞታችን በሞቱ ድል ተነስቶአል፤ እሱን በኩር አድርገን ሁላችን እንነሳለን፤ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ሞት በሰው ልጆች ላይ ኃይልና ሥልጣን የለውም፤ መቃብርም ይዞ ማስቀረት አይችልም፤ በጻድቃንና በኃጥአን የፍርድ አደባባይ የክብርና ወይም የሐሣር ትንሣኤ ለመነሳት ምርጫውና ውሳኔው የእያንዳንዳችን ስለሆነ የክብር ትንሣኤ ለመነሳትና ክርስቶስ የሚያወርሰንን የልጅነት ክብር ለማግኘት ምርጫችንን ከወዲሁ ማስተካከል ይኖርብናል። ✥



www.ethiopianorthodox.org